# ይድረስ ለ-ወክንድ

## ከራሴ ቀና አልኩኝ

የዘገየህ መስሎኝ ክነድህ የታጠፈ
የናትህ ቤት ለማኝ ሆድህ ያኮረፈ
የጋመ ፍም ባመድ እንደተዳፈነ
ያንተም ክንድ ሳይተኛ በቀን የታፈነ
ድምጽህን ሰማሁኝ ህልሜም እውን ሆነ !

ሥጋት ባይኖርብኝ ፍራቻ ባላውቅም
ወትሮስ መች አጣሁት የክንድህን አቅም
ጡንቻህ ሲነቃነቅ ጠረንህ ቢሸተኝ
ካንቀላፋሁበት ተራሴ ቀናልኩኝ

ግርም ያደርገኛል ያሰብኩት እንደሆን
ሰው በገዛ ሀገሩ ስደተኛ ሲሆን
ተብሎ ሲዘፈን አልገባኝም ነበር
ለካ ሠው ባገሩ ሥደተኛ ነበር

ያባት ያያቶቼ ሥራቸው ታወሰኝ
የክንድህ ትኩሳት ግሎ ቀስቀሰኝ

ዐብረውኝ የተኙ በደል  ያልነካቸው
የእግዚአብሄር ፍጡራን ጭዳ በጎች ናቸው
.........የእናታችን ቤት አሽከሮች አምጸው
        እርሳሶቻችውን ጠመንጃ አስቀርጸው
        እንደ ትንቢቱ ቃል በምድር ተነሱና
        ቀይ ቀለም ጠጡ ወሃ ጨረሱና
        አንተ ግን ጻፍበት
        ያገርህን ታሪክ የጀግናውን ዝና
        ለእውነት የተሠዋው ወንድምህ ነውና !!!
        ለፍትህ የሞተው ወንድምህ ነውና !!!

ስማኝ ወንድምዬ
ሞቴ ደስታዬ ነው ስቃዬም ደስታዬ
የነጻነት ጽዋ የፍትህ ፋንታዬ
ሞቴ ክብር አለው
ለወንድምህ ሬሳ ....... ሜዳ ላይ ለቀረው
ትግልህ ዋልታ ማገር
ድልህ ግድግዳው ነው
ወኔህ ጣራ ሆኖ
ግብህ መሠረት ነው

ትቢያው ተገፎለት ቁልሉ ተነስቶ
አጽም ሥጋ ለብሶ በስትንፋስ ተሞልቶ
የነፍሳተ ሠማይ መስኮቱ ተከፍቶ
የትንሳዔው ብስራት መለከት ተነፍቶ
በርታ ! ይልሃል ወንድምህ
በቃ ! ይልሃል ወንድምህ
የነጻነት ጓድህ !

ለዘመናት በጭቆና ማቅ
በግፍ ሠንሠለት ታስሬ
ጨቋኙን ልሽር
መብቴን ላስከብር
ተነስቻለሁ ዛሬ
ይሄው ታጥቂያለሁ ዛሬ
በአንድ እንደሚነሳ ተበዝባዡ ሁሉ
በማያወላውል ድሉ
ፍጹም ነው እምነቴ
የትግሉ ነው ህይወቴ
ልጓዝ በድል ጎዳና በወደቁት ጓዶች ፋና
……………………………………
በገጠር ከተማ የወደቀው
ሻማ ሆኖ ለኛ የቀለጠው
ያ ! ወርቃማ ትውልድ ያስረከበን
ያደራው ቃል አለብን …………… !
ስትል ሠማሁና ደስ ቢላት ነፍሴ
ካንቀላፋሁበት ቀናልኩኝ ተራሴ !

መስፍን መሀመድ ከአዶላ ወዩ